2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39902

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢት/መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብሬ ሙሲሳ - በሌሉበት

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ለደንበኛው ለኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ናፍጣና ቤንዚን የጉዞ መድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን ከነዳጁ ውስጥ 31,513 ሊትር የስር ተከሳሾች በሆኑት መኪና ሲጓጓዝ መኪናው ተገልብጦ 18,153 ሊትር የፈሰሰ በመሆኑና የነዳጁን ዋጋ ብር 45,927.09(አርባ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከዘጠኝ ሣንቲም) ለደንበኛው ስለከፈለ ይህንኑ ገንዘብ ከተከሳሾች መኃከል ኃላፊነት ያለበት ተለይቶ እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት አመልክቷል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከክሱ ወጪ የሆኑ ሲሆን ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ጉዳዩ በእርቅ ማለቅ ያለበት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይም በሰጡት መልስ ነዳጁን የጫነው መኪና ባለቤት ስላልሆኑ ኃላፊነት እንደሌለባቸው ከነዳጁ ባለቤት ጋር ያደረጉት የማጓጓዝ ውል አለመኖሩን እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖቹ የኢት/ነዳጅ ድርጅትና የጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ጠይቀዋል፡፡ ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት ክስ የተመሰረተበትን ነዳጅ የጫነው ተሳቢ ነዳጁ ፈሰሰ ከተባለበት ቀን በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ ጭነት መኪና ወደኋላ ተንሸራቶ እየተገለገሉበት ያለውን ነዳጅ የጫነውን ተሳቢ እንዲገለበጥ በማድረጉ ተጠሪ ለጉዳቱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2081(1) እና (2) መሰረት ኃላፊ ናቸው ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ተሳቢውን አደጋው ከመድረሱ በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የለበት በማለት ተጠሪ በክስ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በኢት/ነዳጅ ድርጅትና በጣና ፈሳሽ መጓጓ ዣ ባለንብረቶች ማህበር መኃከል በተደረገው ውል አንቀጽ 18 መሰረት ከውሉ ትርጉምና አፈፃፀም ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሚነሳ አለመግባባት ሁለቱ በመረጧቸው ገላጋይ ዳኞች አማካኝነት እንደሚታይ ስምምነት ተደርጓል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በን/ህ/ቁ 683 ባገኘው የመዳረግ መብት በመሆኑና ይህ የመዳረግ መብት ደንበኛው ባለው መብት ልክ ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የሚነሳው ክርክር በስምምነት ማለቅ ስላለበት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የይግባኝ ሰሚውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው በአመልካች ደንበኛና በጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር መሃከል የተደረገው ውል ተፈፃሚነት የሚኖረው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል ለሚነሳ ክርክር እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አይደለም፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የቀረበው የተረከቡት ነዳጅ ላይ ጉዳት በመድረሱ የአጓጓዥ ኃላፊነት ስላለባቸው በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ውል መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የአመልካች ደንበኛ ከጣና ፈሳሽ መጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ጋር ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ስለተስማማ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በፍ/ቤት ሊታይ አይገባም በሚል የተሰጠው ውሳኔን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪ በህይወት ስለሌሉ ወራሾቻቸው እንዲቀርቡ በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግም ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረተው በተጠሪ የጭነት መኪና እየተሳበ በነበረው ተሳቢ ላይ ተጭኖ የነበረው ነዳጅ ተሳቢው በመገልበጡ ምክንያት ፈሶ ስለባከነ ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ተጠሪ እንዲተኩ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የወሰነው የአመልካች ደንበኛ ከጣና